# የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅትን፣ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅትንና የበጎ አድራጎት ተቋምን ለማቋቋም የወጣ መመሪያ

## ቁጥር 25/2012

## የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅትን፣ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅትንና የበጎ አድራጎት ተቋምን ለማቋቋም የወጣ መመሪያ ቁጥር 25/2012

በማህበር መልክ መደራጀት ሣይኖርባቸው ገንዘባቸውንና ንብረታቸውን በመለገስ ለብቻቸው ወይም በተናጠል በመሆን በአደረጃጀቱ ያልተወሣሠበና ቀላል የአስተዳደር ስልትን የሚከተል የበጎ አራጎት ድርጅት ዓይነት በማቋቋም የበጎ አድራጎት ሥራ መሥራት የሚፈልጉ ሰዎችን መደገፍ፣ ማበረታታትና ለሥራቸውም ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅት እና የአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅትን ለማቋቋም መነሻ ገንዘብ ወይም ንብረት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ መስጠት ሕግ የሚያስገድድ ሲሆን ይህንኑ አነስተኛ መነሻ የገንዘብ መጠን በሕግ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የበጎ አድራጎት ተቋም ከፈረሰ በኂላ የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት ድርጅቱ ያሉበትን ወጪዎችና ዕዳዎች ለመሸፈን በቂ ሆኖ ካልተገኘ ወጪዎቹንና ዕዳዎቹን ለመክፈል የሚያስችል የዋስትና ገንዘብ ወይም ንብረት ድርጅቱ ሲቋቋም የድርጅቱ መሥራች አባላት ማስያዝ ስለሚኖርባቸው ይህንኑ አነስተኛ የዋስትና የገንዘብ መጠን በሕግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 በአንቀጽ 9 (4) እና አንቀጽ 28 (2) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፩. አውጭው አካል

የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ በበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራትን ለመመዝገብና ለማስተዳደር በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 9(4) እና 28(2) በተሠጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### አንቀጽ ፪ አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የዘለቄታ በጐ አድራጐት ድርጅትን ፣ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅትና የበጐ አድራጐት ተቋምን ለማቋቋም የወጣ መመሪያ ቁጥር 25/2012 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ ፫ ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ዉስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር፡-

1. **"አዋጅ"** ማለት የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራትን ለመመዝገብና ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ ቁጥር 621/2001 ነው፡፡
2. **"ደንብ"** ማለት ስለበጐ አድራጐት ድርጅቶች እና ማህበራት ምዝገባና አስተዳደር የወጣ የሚንስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 168/2001 ነው፡፡
3. **"ኤጀንሲ"** ማለት የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ነው፡፡
4. **"ቦርድ"** ማለት የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ቦርድ ማለት ነው፡፡
5. **"ዋና ዳይሬክተር"** ማለት የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡
6. **"የበጎ አድራጎት ሥራዎች"ማለት** በአዋጁ አንቀፅ 14(1)(ሀ-ነ) የተዘረዘሩት የበጐ አድራጐት ዓላማዎች ናቸው፡፡
7. **"የዘለቄታ በጐ አድራጐት ድርጅት"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 16 የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፡፡

8. **"የበጐ አድራጐት ተቋም"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) ላይ የተመለከተውን ትርጓሜ ይይዛል፡፡

9. **"የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 30 ላይ የተመለከተውን ትርጓሜ ይይዛል፡፡

10. በአዋጁና በማስፈጸሚያ ደንቡ ላይ የተቀመጡ ሌሎች ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያ ላይም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

11. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## አንቀጽ ፬ <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ፡-

ሀ. ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች በሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ወይም የአባላት ጥንቅራቸዉ ከአንድ ክልል በላይ በሆኑ ማህበራት፤

ለ. በአንድ ክልል ብቻ የሚሰሩ ቢሆንም በውጭ አገር በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና በኢትዮጵያ ነዋሪዎች በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት፤

ሐ. በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት፤

መ. በአዋጁ አንቀጽ 48 መሰረት በኤጀንሲዉ ቀርበው የማጽደቅ ዉሳኔ የተሰጣቸው የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የዘለቄታ በጐ አድራጐት ድርጅትን፣ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅትና የበጐ አድራጐት ተቋምን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ መስፈርቶች</u>

### ፩. <u>የዘለቄታ በጐ አድራጐት ድርጅትን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ መስፈርቶች</u>

የዘለቄታ በጐ አድራጐት ድርጅትን ለማቋቋም የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1. በአዋጁ አንቀጽ 68(3) እና በደንቡ አንቀጽ 3 መሠረት የተዘጋጀ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች የምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ፣
2. አንድ ወይም ከዚያ በላይ መሥራች፣
3. የመሥራቹ የሕይወት ታሪክ ቅጽ፣ የፓስፖርት መጠን ያለው አንዳንድ ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም የፀና ፓስፖርት ቅጂ (ዋናው ለማመሣከሪያነት)፣
4. መሥራቹ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ከሆነ የታደሰ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ወይም ሰነድ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡
5. በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተረጋገጠ የድርጅቱ መመስረቻ ሰነድ፣
6. ድርጅቱን ለመመስረት የተሰጠው፡-

    ሀ. ንብረት ከሆነ የንብረቱ ዝርዝር መግለጫና ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ ህጋዊ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ፣

    ለ. ገንዘብ ከሆነ የገንዘቡን መጠንና ገንዘቡ ለመመስረት በታሰበው የዘለቄታ በጐ አድራጐት ስም በዝግ ሒሳብ የተቀመጠ መሆኑን የሚያሣይ የባንክ ማረጋገጫ ሰነድ፣

7. ድርጅቱን በበላይነት እንዲመሩና እንዲያስተዳድሩ በመሥራቹ የተሾሙ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ዝርዝርና ከሕይወት ታሪካቸው ቅፅ ጋር የሚያያዝ አንድ አንድ ፓስፖርት መጠን ያለው ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም የፀና የፓስፖርት ቅጂ ዋናውን ለማመሳከሪያነት፣
8. በደንቡ አንቀጽ 6 መሠረት የተዘጋጀ የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ወይም (ኤጀንሲው በአዋጁ አንቀጽ 17 (5) መሠረት ያዘጋጀውን ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ከተፈለገ መጠቀም ይቻላል)::
9. ድርጅቱ ለትግበራ ያዘጋጀው ፕሮጀክት ፕሮፓዛል፣
10. ድርጅቱ ሊጠቀምበት የሚፈልገው አርማ ወይም ምልክት (ካለ)፣
11. በደንቡ የተመለከቱ የምዝገባና ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍያዎች፡፡

## ፮ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅትን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ ቁጥር (1)፣ (2)፣ (3)፣ (4)፣ (6)፣ (8)፣ (9)፣ (10)፣ (11) የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅትን ለመመስረት የሚከተሉት መስፈርቶችም በተጨማሪነት መካተት ይኖርባቸዋል፡

1. በአዋጁ አንቀጽ 6 (1) (ሸ) መሠረት በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተረጋገጠ የድርጅቱ የአደራ መስጫ ሰነድ ወይም (ኤጀንሲው ያዘጋጀውን ሞዴል የአደራ መስጫ ሰነድ እንደ መነሻነት መጠቀም ይቻላል፡፡)
2. ድርጅቱን በበላይነት እንዲመሩና እንዲያስተዳድሩ በመሥራቹ የተሾሙ የአደራ ጠባቂዎች አባላት ዝርዝርና ከሕይወት ታሪክ ቅፃቸው ጋር የሚያያዝ አንዳንድ ፓስፖርት መጠን ያለው ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም የፀና ፓስፖርት ቅጅ ጋር (ዋናው ለማመሳከሪያነት ይቀርባል፡፡)

## ፯. የዘለቄታና የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅትን ለማቋቋም የሚያስፈልግ አንስተኛ የገንዘብ መጠን

1. የዘለቄታ ወይም የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅትን ለማቋቋም የሚፈልግ ሰው ቢያንስ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ) ያላነሰ ገንዘብ ማስያዝ ይጠበቅበታል፡፡
2. ከላይ የተመለከተውን ገንዘብ አመልካች ድርጅቱ ሕጋዊ ሰውነት እስከሚያገኝ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ ማንኛውም ባንክ ለመመስረት በታሰበው የዘለቄታ በጐ አድራጐት ድርጅት ወይም በአደራ በጐ አድራጐት ስም በዝግ ሒሳብ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡
3. ከላይ የተመለከተው ገንዘብ በባንክ እንዲቀመጥ መሥራቹ ወይም የመሥራቹ ሕጋዊ ተወካይ ለሚፈልገው ባንክ ኤጀንሲው  የድጋፍ ደብዳቤ ይፅፋል፡፡
4. መሥራቹ ወይም የመሥራቹ ተወካይ ገንዘቡ በዝግ ሒሳብ የተቀመጠ ስለመሆኑ የሚገልጽ የባንክ ማረጋገጫ ሰነድ ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
5. በዝግ ሒሳብ የተቀመጠው ገንዘብ አመልካች የዘለቄታ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም የአደራው የበጐ አድራጐት ድርጅት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ

Comment [P1]: እጅግ በጣምበዝቷል፡፡

ሕጋዊ የምዝገባ ሰርተፊኬት ካገኘ በኋላ በኤጀንሲው ትዕዛዝ እንዲለቀቅ እና ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

## ፰. የዘለቄታ ወይም የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅትን ለመመስረት ስለሚሰጥ ንብረት

1. የንብረቱ ዋጋ በኤጀንሲውና በመሥራቹ ወይም በመሥራቹ ሕጋዊ ተወካይ የጋራ ሥምምነት በተመረጠ የንብረት ገማች ባለሞያ ወይም ህጋዊ የንብረት ግመታ በሚያስፈጽሙ መንግስታዊ ተቋማት ወይም በሚመለከታቸው ህጋዊ አካላት በወቅቱ የገበያ ዋጋ በገንዘብ ተተምኖ መቅረብ የሚኖርበት ሲሆን ግምቱ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ) ማነስ የለበትም፡፡
2. ንብረቱ ከዕዳና ዕገዳ ነፃ ሥለመሆኑና የመሥራቹ ሕጋዊ ንብረት ስለመሆኑ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተረጋገጠ ሰነድ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. በአዋጁ አንቀጽ 6 (1) (ሸ) መሠረት የዘለቄታ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ የተቋቋመበት ሕጋዊ መመስረቻ ሰነድም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት መረጋገጥና መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

**Comment [P2]:** ንብረት ከሆነ የዋጋ ግምቱ ይህን ያህል መሆኑ አስፈላጊነቱ ምኑ ላይ ነው ፡

**Comment [P3]:** ይህን የማድረግ ሥልጣን የሰ/ማማጽ/ቤት ነውን

## ፱. የበጐ አድራጐት ተቋምን ለመመስረት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

በአዋጁ አንቀጽ 68 (3) እና በደንቡ አንቀጽ 3 መሠረት የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው የበጐ አድራጐት ተቋምን ለማቋቋም የሚከተሉት መስፈርቶችም መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1. የበጐ አድራጐት ድርጅቶች የምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ፣
2. ሦስትና ከዚያ በላይ የሆኑ መሥራቾች፣ የመሥራቾች የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም የፀና ፓስፖርት ቅጅና ዋናውን ለማመሳከሪያነት፣ ከአንዳንድ ጉርድ ፎቶ ግራፍ ጋር፣
3. መሥራቹ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ከሆነ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም ሰነድ፣

4. በደንቡ አንቀጽ 6 መሠረት ደረጃውን ጠብቆ የተዘጋጀ መተዳደሪያ ደንብ ወይም በኤጀንሲው የተዘጋጀውን ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ መጠቀም ከተፈለገ በመስራቾች የተፈረመ የስምምነት ቃለ ጉባኤ፡፡
5. ለትግበራ የተዘጋጀ ኘሮጀክት ኘሮፖዛል፣
6. የድርጅቱ መመስረቻ ሠነድ፣
7. መሥራቾች ድርጅቱን ለመመስረት የሚያሲዙት፡-
   ሀ. ንብረት ከሆነ የንብረቱ ዝርዝር መግለጫና የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ፣
   ለ. ገንዘብ ከሆነ የገንዘቡ መጠንና ገንዘቡ በዝግ ሒሳብ የተቀመጠ መሆኑን የሚያሣይ የባንክ ማረጋገጫ ሠነድ፣
8. በደንቡ የተመለከቱ ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍያዎች፡፡

## ፲. <u>የበጐ አድራጐት ተቋምን ለመመስረት የሚያስፈልግ አነስተኛ የዋስትና ገንዘብ መጠን</u>

1. የበጐ አድራጐት ተቋምን ለማቋቋም የሚፈልጉ መሥራቾች ቢያንስ ከብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺ) የማያንስ ገንዘብ በዋስትና ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡
2. ከላይ የተመለከተው ገንዘብ የድርጅቱ ሕጋዊ ሰውነት ተጠብቆ እስከሚቆይ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ ባንክ በዝግ ሒሳብ ይቀመጣል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው ቢኖርም የገንዘብ አቀማመጡን በተመለከተ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ያወጣቸውን ሕጎች አፈፃፀም የሚያስቀር አይሆንም፡፡
4. ከላይ የተመለከተውን ገንዘብ በዝግ ሒሳብ ለማስቀመጥ መሥራቾቹ ለኤጀንሲው ሲያመለክቱ መስራቾች በመረጡት ባንክ እንዲቀመጥላቸው የድጋፍ ደብዳቤ ይፃፍላቸዋል፡፡
5. መሥራቾች ገንዘቡ በዝግ ሒሳብ የተቀመጠ ስለመሆኑ የሚገልጽ የባንክ ማረጋገጫ ሰነድ ለኤጀንሲው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
6. ገንዘቡን ያለኤጀንሲው ውሳኔ ወይም ፈቃድ ከባንክ ማውጣት አይቻልም፡፡

**Comment [P4]:** What is this? It seems a business organization. It doesn't attract any person to establish this kind of organization.

**Comment [P5]:** This article wrongly interpreted the provision of the proclamation. This is not the intention of the proclamation. The intention of the proclamation is to oblige the founders to sign a commitment to cover a defined amount of money in case the organization became bankrupt. /አዋጅ አ፣ 28/1/

## ፲፩. የበጐ አድራጐት ተቋምን ለመመስረት በዋስትና ስለሚያዝ ንብረት

1. የንብረቱ ዋጋ በኤጀንሲውና በመሥራቾቹ የጋራ ሥምምነት በተመረጠ የንብረት ገማች ባለሞያ ወይም ህጋዊ የንብረት ግመታ በሚያስፈጽሙ መንግስታዊ ተቋማት ወይም በሚመለከታቸው ህጋዊ አካላት በወቅቱ የገበያ ዋጋ በገንዘብ ተተምኖ መቅረብ የሚኖርበት ሲሆን ግምቱ ከብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺ) ማነስ የለበትም፡፡
2. ንብረቱ ከዕዳና ዕገዳ ነፃ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ሠነድ ከሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት መቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. የባለቤትነት ማረጋገጫ ሠነዱ በሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት ተረጋግጦ የተሰጠው ሰነድ ዋናው በኤጀንሲው ጽ/ቤት ተጠብቆ ይቆያል፡፡
4. ንብረቱ ሊበላሽ ይችላል ወይም ለማስተዳደር ያስቸግራል ወይም ዋጋው ሊቀንስ ይችላል ተብሎ ከተገመተ በኤጀንሲውና በመሥራቾቹ ሥምምነት በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተሽጦ ገንዘቡ በዝግ ሒሳብ በድርጅቱ ሥም እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡
5. በዝግ ሒሳብ የተቀመጠውን ገንዘብ ያለ ኤጀንሲው ፈቃድ ማውጣት አይቻልም፡፡

Comment [P6]: What is the rational behind this amount of money? Should it be decided case by case?

## ፲፪. የዋስትና ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ዋነኛ ዓላማ

1. የበጐ አድራጐት ተቋሙ ከፈረሰ የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት የድርጅቱን ዕዳዎችና ወጪዎች እንዲሁም የድርጅቱን ሀብት ለማጣራት፣ ለማስተላለፍና ለማስወገድ በቂ ሆኖ ካልተገኘ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 10 እና 11 የተመለከተው ገንዘብ ወይም ንብረት ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡
2. በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ወይም ንብረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱትን ወጪዎችና ዕዳዎች መሸፈን ካልቻለ እያንዳንዱ አባል በአዋጁ አንቀጽ 27(1) መሠረት በግሉ ተጠያቂ ይሆናል፡፡
3. የበጐ አድራጐት ተቋሙ በሕግ አግባብ ከፈረሰ በኋላ ያለው ገንዘብና ንብረት ያለበትን ወጪና ዕዳ እንዲሁም ንብረቱን ለማጣራት፣ ለማስተላለፍ እና ለማስወገድ የሚወጣውን ወጪ ሙሉ በሙሉ ከሸፈነ በዋስትና የተያዘው

Comment [P7]: ከአዋጁ 28 /1/ ጋር ይጣረሳል፤ ከገቡት ግዴታ በላይ ኃላፊ ሊሆኑ አይገባም፤

ገንዘብ ወይም ንብረት ተመሣሣይ ዓላማ ላለው የበጎ አድራጎት ድርጅት ይተላለፋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፫. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ባህላዊ አሰራር ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### ፲፬. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቦርዱ ፀድቆ ከወጣበት ከሐምሌ 9 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 2003 ዓ.ም**

**ዓሊ ሲራጅ**
**የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ**
**ዋና ዳይሬክተር**